የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ መጋቢት ፬ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 22
ADDIS ABABA, 13rd, March, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፩ /፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ዓይነሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሁፍ ህትመት ሥራዎች ተደራሽነትን ለማመቻቸት የወጣውን የማራከሽ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ.................................................ገጽ ፲፪ሺ፪፻፸

## CONTENT

PROCLAMATION No. 1181/2020

Marrakesh Treaty to facilitate access to published works for persons who are blind, visually impaired, and print disabled Ratification Proclamation……………………………Page 12270

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፩/፪ሺ፲፪**

**<u>ዓይነሥውራን፣ ለንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሁፍ ህትመት ሥራዎች ተደራሽነትን ለማመቻቸት የወጣውን የማራከሽ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ዓይነሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሁፍ ህትመት ሥራዎችን ተደራሽነትን ለማመቻቸት የወጣው የማራከሽ ስምምነት ሐምሌ ፳ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በማራካሽ ስምምነት የተደረሰበት በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ስምምነቱን የፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት የካቲት ፭ ቀን

**PROCLAMATION NO. 1181/2020**

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE MARRAKESH TREATY TO FACILITATE ACCESS TO PUBLISHED WORKS FOR PERSONS WHO ARE BLIND, VIRTUALLY IMPAIRED, AND PRINT DISABLED</u>**

**WHEREAS,** the Marrakesh treaty to facilitate access to published works for persons who are blind, visually impaired, and print disabledwas adopted in Marekesh on 27 July 2013;

**WHEREAS,** the Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia signed the Marrakesh Treaty on 28 June 2013;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 13th day of February , 2020;

፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩.<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ዓይነሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሁፍ ህትመት ሥራዎች ተደራሽነትን ለማመቻቸት የወጣውን የማራከሽ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፩/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪.<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

ዓይነሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሁፍ ህትመት ሥራዎችን ተደራሽነትን ለማመቻቸት ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም የወጣው የማራከሽ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫.<u>አስፈጻሚ አካል</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአእምሯዊ ንብረት ጽህፈት ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፕሮቶኮሉን የማስፈፀም እና የመከታተል የጋራ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡

## ፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THEREFORE,** in accordance w 12271 5 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the " Marrakesh Treaty to facilitate access to published works for persons who are blind, visually impaired, or otherwise print disabled Ratification Proclamation No· 1181/2020"

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Marrakesh Treaty to facilitate access to published works for persons who are blind, visually impaired, or otherwise print disabledhas been signed in Marekesh on 28th June 2013 is hereby ratified.

## 3. <u>Implementing Organ</u>

The Ministry of Education and the Ethiopian Intellectual Property Office of the Federal Democratic Republic of Ethiopia are given the responsibility to cooperate with other relevant organs to implement and follow-up this Convention.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come into force up on publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of March , 2020·**

**SAHLE-WORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**